የTCTዝብላክ ኢትዮጵያ

# ሳምንታዊ ጋዜጣ

Purpose Black ETHIOPIA

2015 ሐምሌ ቅጽ 1 ቁጥር 20

## በቲኤስኤም ሁለተኛ ዙር የማስተወቂያ ዋጋ አክሲዮን ሽያጭ የተዘጋጀውን ልዩ አጋጣሚ ዕድለኞች የጊዜ ገደቡ ሳይጠናቀቅ እንዲጠቀሙ ጥሪ ቀረበ።

ጥሪውን ያቀረቡት የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ በታወር ሼር ሆልደር ሞዴል የአክሲዮን ሥርዓት ከሐምሌ 1-16 የተዘጋጀው የሁለተኛ ዙር የ3.5 ሚሊዮን ብር አክሲዮን ሽያጭ መርሐግብር እስከ ሐምሌ 30 መራዘሙን ይፋ ማድረጋቸውን ተከትሎ ባስተላለፉት መልእክት ሲሆን አክሲዮኑን መግዛት መቻል ሦስት ተደራራቢ ዕድሎችን መጠቀም የሚቻልበት ልዩ አጋጣሚ መሆኑን አውስተዋል።




> በቅድመ ክፍያ 3 ሚሊየን ብር ተከፍሎ ቀሪው 500 ሺህ ብር በ5 ዓመት ጊዜ ከወለድ ነጻ በሆነ ሒደት በየወሩ የሚከፈልበት መንገድ የተመቻቸለት ይህ የቲኤስኤም ሁለተኛ ዙር አክሲዮን ሽያጭ መርሐግብር ለ750 ቀዳሚ ዕድለኞች ብቻ መዘጋጀቱን ያነሡት ዋና ሥራ አስፈጻሚው ዕድሉ በመሃል ሜክሲኮ የቢጂአይ ኢትዮጵያ ዋና መሥሪያ ቤት ይገኝበት በነበረው ይዞታ ላይ ከታሪካዊው የከገበሬው ታወር አቅራቢያ በሚገነባው 8B+G+60 ሕንጻ ላይ 100 ካሬ ላይ የሚያርፍ የባለ 3 መኝታ መኖሪያ ቤት ባለቤት መሆን እንደሚያስችልም ጠቅሰዋል።

በተጨማሪም አክሲዮኑ አጋጣሚውን የሚጠቀሙ ባለአክሲዮኖችን የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ባለቤት ከማድረጉ ባለፈ የከገበሬው ታወር ግንባታ ሲጠናቀቅ ከሚገኘው ገቢ እንዲሁም ኩባንያው በተሠማራባቸው የግብርና፣ የማቀነባበሪያ፣ የኢኮሜርስ፣ የምርት ስርጭት፣ የችርቻሮ ማከፋፈያ የቢዝነስ ሞዴሎች ከሚያገኘው አጠቃላይ ገቢ ትርፍ ተከፋይ መሆን ማስቻሉም ተገልጿል።

ከዚያም ባለፈ በሁለተኛው የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ባለአክሲዮኖች ጉባዔ የኩባንያው አጠቃላይ ካፒታል 5 ቢሊዮን ብር ሲደርስ የአንድ አክሲዮን መሸጫ ዋጋ ወደ 3 መቶ ብር እንዲያድግ በተላፈው ውሳኔ መሠረት በቲኤስኤም አክሲዮን በ3.5 ሚሊዮን ብር ዋጋ የገዙት አክሲዮን በ3 እጥፍ የሚያድግ መሆኑ አጋጣሚውን ልዩ እና ሊታለፍ የማይገባው እንደሚደርገው ተጠቁሟል።

## TCTዝብላክ ኢትዮጵያ በሁለት ዓመታት ውስጥ ያስመዘገበው ስኬት በአገራችን በግሉ ዘርፍ ከተሠማሩ ሌሎች ኩባንያዎች አንጻር ቀዳሚ እንደሚያደርገው ተገለጸ።

ከሁለት ዓመታት በፊት በሰሜን አሜሪካ በቀድሞው የዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ መሥራችና ባለቤት ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ ሐሳብ አመንጪነት በአክሲዮን ማኅበርነት ተቋቁሞ ዘርፈ ብዙ እምርታዎች ያስመዘገበው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የሁለት ዓመታት ጉዞውን በልዩ ሁኔት ለመዘከር ቅድመ ዝግጅት ላይ መሆኑ ተገለጸ።

“ከሚሊዮን ወደ ቢሊዮን በሁለት ዓመት ብቻ ቃልን በተግባር” በሚል መሪ ቃል የፊታችን ሐምሌ 30 ቀን 2015 ዓ.ም በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ ከቀኑ 7፡00 ሰዓት እስከ ምሽት 2፡00 ሰዓት የሚከናወነው ይህ የሁለተኛ ዓመት የምሥረታ ክብረ በዓል ኩባንያው የተጓዘባቸውን መንገዶች የሚያወሱ መሰናዶዎች እንደሚቀርቡበትም ታውቋል።

Purpose Black ETHIOPIA

በሦስት ዓበይት ክፍሎች የሚካሔደው የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ 2ኛ ዓመት ልዩ ሁነት ተቋሙ የተሰማራባቸውን ዋና ዋና ፕሮጀክቶች በዓውደ ርዕይ መልክ ለሚጋበዙት ታዳሚ እንግዶች ማስጎብኘት በቀዳሚነት የሚከናወን ሲሆን በማስከተል ከመድረክ ልዩ ልዩ አስተማሪና አዝናኝ ዝግጅቶች ቀርበው በስተመጨረሻም ለእንግዶች የእራት ግብዣ ተከናውኖ የመርሐግብሩ ፍጻሜ እንደሚሆን ተገልጿል።

በዕለቱ የሚቀርበው ዓውደ ርዕይ ኩባንያው በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ውስጥ ለማሳካት እየተንቀሳቀሰባቸው የሚገኙትን በኢትዮጵያ ግዙፍ የግብርና ክላስተር የሚያስተዳደር ተቋም፣ በኢትዮጵያ ትልቁ የዕለት ፍጆታዎች አቅራቢ ኩባንያ፣ በኢትዮጵያ ትልቁ የግብርና ውጤቶች ማቀነባበሪያ ተቋም፣ በኢትዮጵያ ትልቁ የምርቶች ማከፋፈያ ችርቻሮ ሱቆች የሚያስተዳደር ኩባንያ፣ በኢትዮጵያ ትልቁ የደንበኞች የዱቤ አገልግሎት አቅራቢ ተቋም፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ ትልቁ የዘመናዊ ግብርና ልማት የሚያካሒድ ኩባንያ ከመሆን አንጻር የደረሰባቸውን እምርታዎች የሚያስቃኝ እንደሚሆን ይጠበቃል።

በሁነቱ ላይ እንደ ፐርፐዝብላክ ኬርስ ፋውንዴሽን፣ ትራክተር ለገበሬው፣ ከገበሬው ሪል አስቴት፣ እንዲሁም ከገበሬው የቴሌቪዥን ጣቢያ የተሰኙት ፕሮጀክቶች በይፋ እንደሚተዋወቁ ተገልጿል።

ሁነቱ በሚካሄድበት መርሐግብር ላይ ታላላቅ የመንግሥት ባለስልጣናትን ጨምሮ፣ የአጋር ተቋማት ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች፣ ባለሃብቶች፣ የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ባለአክሲየኖች እና የኩባንያው ሠራተኞች በክብር እንግድነት እንደሚታደሙ ተነግሯል። በግብርና፣ በግብርና ውጤቶች ማቀነባበር፣ በኢኮሜርስ፣ በኩታ ገጠም እርሻ መርሐግብር፣ በችርቻሮ ሱቆች፣ በምርት ስርጭት አገልግሎቶች ላይ እየተንቀሳቀሰ የሚገኘው ኩባንያው ከሁለት ዓመት አስቀድሞ በኢትዮጵያ ቢዝነስ ኢንዱስትሪ መሠማራት በጀመረበት ወቅት ከተነሣበት የ1 ሚሊዮን ብር ካፒታል አሁን ላይ አጠቃላይ ካፒታሉን ወደ 2 ቢሊዮን ብር ማሳደግ ከመቻሉ ባለፈ ሁለንተናዊ እድገትን ማስመዝገቡም ይፋ ተደርጓል።

**TCTዝብላክ ኢትዮጵያ የሚያዘጋጃቸው ሁነቶች በተሳካ ሁኔታ እንዲከናወኑ የኩባንያው የሁነት ዝግጅት ክፍል ሚና ጉልህ መሆኑ ተገለጸ።**

ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶቹን እና መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴዎቹን ለማስተዋወቅ የተለያዩ ሁነቶችን የሚያዘጋጀው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ትሬዲንግ ኢ.ማ. የሚያካሒዳቸው መርሐግብሮች ግባቸውን መምታት እንዲችሉ ከማድረግ አንጻር የሁነት ዝግጅት ክፍሉ ከዋና ሥራ አስፈጻሚ ቢሮ እና ሌሎች የሥራ ክፍሎች ጋር በመቀናጀት የሚያበረክተው አስተዋጽዖ ወሳኝ መሆኑን የክፍሉ ዳይሬክተር ወ/ት አልማዝ አረጋ ገልጸዋል።

Purpose Black ETHIOPIA

ክፍሉ ከተለያዩ የኩባንያው ዘርፎች በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት በዝርዝር ጉዳዮቹ ላይ በጥልቀት በመወያየት፣ እንደየዝግጅቱ ስፋት እና ዓይነት አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶችን ያደርጋል ያሉት ኃላፊዋ በተቋሙ ውስጥ የሚከናወኑትን ሁነቶች የኩባንያውን መልካም ስም መጠበቅ የሚያስችሉ እንዲሆኑ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኙም አስረድተዋል።


የሁነት ክፍሉ ከሌሎች የሥራ ክፍሎች ጋር በትብብር ካዘጋጃቸው መሰናዶች መካከልም ጥር 6 ቀን 2015 ዓ.ም በሚሊኒየም አዳራሽ የተከናወነው የኩባንያው ባለአክሲዮኖች ሁለተኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ፣ የመጀመሪያው ዙር የከገበሬው ሕንጻ አክሲዮን ሽያጭ፣ የከገበሬው ኢኮሜርስ አዳዲስ ፕሮጀክቶች ማስጀመሪያ እና የከገበሬው ምርት ስርጭት ኮርፖሬት የውይይት እና ምርት ቅምሻ መርሐግብሮች ተጠቃሽ ሲሆኑ ከመድረክ ዝግጅት እና አዳራሽ የማስዋብ ተግባራት በተጨማሪ ክፍሉ በእንግዶች ምዝገባ፣ አቀባበልና መስተንግዶ በኩል ከፍተኛ ተሳትፎ ማድረጉ ተነስቷል።

በተጨማሪም ኩባንያው በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በሚሰጣቸው ጋዜጣዊ መግለጫዎች እና በሚደረጉ ወርኃዊ ስብሰባዎች ላይ የማስተባበር እና ቀዳሚ ተሳታፊ የመሆን ድርሻውን እየተወጣ እንደሚገን የጠቀሱት ወ/ሪት አልማዝ የኩባንያው ሁነት ዝግጅት ከሌሎች ክፍሎች በተለየ ከኩባንያው የማርኬቲንግ፣ ኮሚኒኬሽን እና ጠቅላላ አገልግሎት ክፍል ጋር በቅርበት እየሠራ በዋናው መሥሪያ ቤትና በሆቴሎች እንዲሁም አዳራሾች በተደረጉ ዝግጅቶች ላይ በቅንጅት ውጤታማ መርሐግብሮችን ማከናወን መቻሉን አስታውቀዋል።

በቅርቡም ኩባንያው ሁለተኛ ዓመት የምሥረታ በዓሉን ለማክበር በዝግጅት ላይ መሆኑን ተከትሎ ለዚህ መርሐግብር ለእንግዶች የጥሪ ካርድ ከማዘጋጀት እና ማሰራጨት ጀምሮ ሌሎች የማስታወቂያ ሥራዎች የተጀመሩ ሲሆን በዕለቱ በቦታው ለሚቀርቡ ዝግጅቶች ከኩባንያው የሚዲያ እና ማርኬቲንግ ክፍል እንዲሁም ከተቋሙ ውጪ ከሚመጡ የሁነት አዘጋጅ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት መርሐግብሩ የተሳካ እንዲሆን አስፈላጊ የሆኑ ቅድመዝግጅቶች መጀመራቸውም ተገልጿል።

**ሳፋሪኮም የTCTዝብላክ ኢትዮጵያን አገልግሎቶች በመላው አፍሪካ ተደራሽ ማድረግ የሚቻልበት አማራጭ መኖሩን ገለጸ።**

የቴሌኮም ኩባንያው ባሳለፍነው ረቡዕ ሐምሌ 13 ቀን 2015 ዓ.ም በፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ዋና መሥሪያ ቤት በመገኘት ሁለቱ ተቋማት በጋራ መሥራት በሚችሉባቸው ነጥቦች ዙሪያ በተወያዩበት ወቅት ነው የፐርፐዝብላክን የአገልግሎት ተደራሽነት አድማስ ከማስፋት አንጻር አማራጭ ይዞ መቅረቡን ይፋ ያደረገው።



ምስል በነብዩ ዳንኤል

**“በዕለቱም የቴሌኮም ኩባንያውን በመወከል የሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ኮርፖሬት አካውንት ማናጀር ካሚላ ሙሰማ፣ የኩባንያው ኢንተርፕራይዝ ቢዝነስ ማኔጀር አቶ ፍስሐ ዘመኑ እና የኤም-ፔሳ ፕሮዳክት ማኔጀር ሲሪሌ ፋሉላ በውይይቱ የተሳተፉ ሲሆን በTCTዝብላክ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ አማካኝነት ስለኩባንያው ገለጻ ተደርጎላቸዋል።**

በወርኃ መስከረም 2015 ዓ.ም. በይፋ በኢትዮጵያ አገልግሎት መስጠት የጀመረው የኬንያው ግዙፍ የቴሌኮም ኩባንያ ሳፋሪኮም በአገራችን በዘርፉ በርካታ ለውጦችን ለማስተዋወቅ እንቅስቃሴ ላይ ከመሆኑ ባለፈ ከተለያዩ መንግሥታዊ እና የግል ተቋማት ጋር በጥምረት መሥራት የሚችልበትን ሥርዓት በመዘርጋት ላይ እንደሚገኝ ተገልጿል።

የቴሌኮም ድርጅቱ የክፍያ መተግበሪያ እና ገንዘብ ማስተላለፊያ የሆነውን ኤም ፔሳ እና ሌሎችንም አገልግሎቶች በተመለከተ የሳፋሪኮም ባለሙያዎች በሰጡት ማብራሪያም የከገበሬውን ምርትና አገልግሎቶች ለማስተዋወቅ እና ለገበያ ማቅረብ የሚቻልባቸውን አማራጮች አስተዋውቀዋል።

ምስል በኑብዩ ዳንኤል



“

**በኢትዮጵያ የሞባይል ገንዘብ ማንቀሳቀሻ አገልግሎቶች መስፋፋታቸውን ተከትሎ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓቱ ላይ ከፍተኛ መነቃቃት ተስተዉሏል ያሉት ተወካዮቹ ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በጀመረው የበይነ መረብ ግብይት ላይ ተግባራዊ እያደረገው ያለውን ዲጂታል ክፍያ ለመቀላቀል ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ፍላጎት ያለው መሆኑንም ተናግረዋል።**

ሁለቱም ኩባንያዎች ከተቋቋሙ ከሁለት ዓመት ያልበለጠ እድሜ ማስቆጠራቸው እና ለመላው ጥቁር ማኅበረሰብ ጥራቱን የጠበቀ ምርትና አገልግሎት ለማቅረብ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን እያከናወኑ መሆናቸው በውይይቱ ላይ የተነሣ ሲሆን ይህንንም ጥረት ውጤታማ ለማድረግ በጋራ መሥራታቸው ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ተጠቅሷል።

በተለይም የከገበሬው ኢኮሜርስ ውጤት በሆነው ቬንደር ማኔጅመንት ሲስተም እና የጥሪ ማእከል አማካኝነት የኩባንያውን ተደራሽነት ለማስፋት ሳፋሪኮም አገልግሎቱን በሚሰጥባቸው የአፍሪካ አገራት ፐርፐዝብላክን ማስተዋወቅ የሚቻልባቸው ነጥቦች በዝርዝር ተነሥተዋል።

ምስል በኑብዩ ዳንኤል



ከዚህ ጋር ተያይዞም ሳፋሪኮም በተለያዩ መደብሮች መግቢያ ላይ ለማስታወቂያ የሚጠቀምባቸው ተንቀሳቃሽ ሱቆች የሁለቱንም ተቋማት ምርትና አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል ምክረ ሐሳብ የቀረበ ሲሆን በሁሉም የከገበሬው ሱቆች የሳፋሪኮም ሲምካርዶች እንዲሸጡ ስምምነት ላይ ተደርሷል።

በኢንተርኔት ክላውድ አማካኝነት ከገበሬው የጥሪ መቀበያ በአፍሪካ አገራት የመረጃ ማእከል ማደራጀት ሳያስፈልገው ከሳፋሪኮም ሲስተም ጋር በማስተሳሰር ብቻ ደንበኞችን ማስተናገድ የሚችልበት መንገድ መኖሩን ያመላከቱት ባለሞያዎቹ ደንበኞች በአጭር ቁጥር በመደወል ትእዛዝ መፈጸም ከሚያስችላቸው የኔትዎርክ ዝርጋታ በተጨማሪ በኤም ፔሳ ሱፐር አፕ kegeberew.com ን በማካተት ተደራሽነቱን ማስፋት ይቻላል ብለዋል።

በጥቂት ቀናት ውስጥም የጋራ መግባቢያ ሰነድ በመፈራረም ሁለቱ ኩባንያዎች በይፋ በጋራ መሥራት የሚጀምሩ መሆኑ እና የመላው አፍሪካን አህጉር የኢኮኖሚ እና የቴክኖሎጂ ምህዳር ለማስፋት እንደሚንቀሳቀሱ ይፋ ተደርጓል።

## የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያን ተሞክሮ በመላው አፍሪካ ለማስፋት የሚቻልበት ሒደት ተጠናክሮ መቀጠሉ ተገለጸ።

ከደቡብ ሱዳን፣ ሶማሊላንድ እና ታንዛኒያ አገራት የመጡ ልዑካን የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያን ልምድና ተሞክሮ ለመቅሰም እንዲሁም በጋራ ለመሥራት በሚያስችሏቸው ነጥቦች ዙሪያ ለመመካከር በኢትዮጵያ ያደረጉትን የሦስት ቀናት ቆይታ አጠናቅቀው ወደየአገራቸው መመለሳቸውን በፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ሙሽመንት ክፍል ኃላፊ አቶ ኢዮብ ዳንኤል አስታወቁ።

አቶ ኢዮብ እንደገለጹት የፐርፐዝብላክ ግሎባልን ተነሣሽነት ራዕይ በመጋራት የሁሉም አፍሪካ አገራት ዜጎች ያላቸውን የተፈጥሮ ሃብት፣ የገንዘብ እና ሌሎች አቅሞቻቸውን በማቀናጀት ኢኮኖሚያዊ ብቃታቸውን እንዲገነቡ በማለም የፐርፐዝብላክ አፍሪካ ንቅናቄ የተጀመረ መሆኑን ገልጸዋል።

Purpose Black ETHIOPIA

የሦስቱ ሀገራት ተወካዮች ከፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ እና ሌሎች የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ጋር ባከናወኑት የትውውቅ እና የውይይት መርሐግብር የፐርፐዝብላክ መሥራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ ጠለቅ ያለ ገለጻ የሰጡ ሲሆን አቶ አማኑኤል መለሰ የከገበሬው ኢኮሜርስን በተመለከተ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

የከገበሬው የጥሪ ማእከልን ጨምሮ የኩባንያውን የሥራ እንቅስቃሴ የተመለከቱት እንግዶቹ በሰሚት የከገበሬው ሱቅ እና ጅስ ባር በመገኘትም ቅኝት አድርገው የሱቆቹን አደረጃጀት በተመለከተ በከገበሬው ምርት ስርጭት ዋና ኃላፊ ቀሲስ አንዱዓለም ገረመው ገለጻ ተደርጎላቸዋል።

ተወካዮቹ በተጨማሪም በበቆጂ እና ስሬ ወረዳዎች እየተከናወኑ ያሉ የእርሻ ሥራዎችን በመዘዋወር የጎበኙ ሲሆን በጉብኝታቸው መጨረሻም የጋራ መግባቢያ ሰነድ ተፈራርመው የኩባንያውን ከገበሬው የተቀናጀ ግብርና ማስፋፊያ፣ ኢኮሜርስ፣ ኤክስፖርት እና ሌሎች ክፍሎች አተገባበር በማንሣት በጋራ መሥራት ስሚችሉባቸው ዘርፎች ዙሪያ መክረዋል።

በኢትዮጵያ ካለው የፐርፐዝብላክ ልምድ እና ተሞክሮ በመነሣት በቅርቡ በሦስቱም አገራት የሚጀመረውን የፐርፐዝብላክ ተነሣሽነት ትግበራ በተመለከተ አቅጣጫዎችን አስቀምጠው በቀጣይ ተነሣሽነቱን በመጋራት ዜጎች ባለቤት የሆኑበት ተቋም ከማደራጀት ባሻገር የፐርፐዝብላክን ምርትና አገልግሎቶች ወደአገራቸው በማስገባት ነጻ አኅጉራዊ የንግድ ቀጠና ትስስርን የመመስረት ውጥንን እውን ለማድረግ ፐርፐዝብላክን እንደ መነሻ መጠቀም እንደሚቻል አመላክተዋል።




ዋና አዘጋጅ፡ ሰላማዊት ደበበ
ሲንየር ሪፖርተር፡ ጌታባለው ገ/ሐና
ሪፖርተር፡ ኤደን ደነቀ

**ለበለጠ መረጃ**

ለገንተራ ነጋዴዎች ህብረት ህንጻ 5ተኛ ፎቅ

+251-946-545454/
+251-925922222/
+251-925822222

7151

www.purposeblackethiopia.com